የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፯
አዲስ አበባ ታህሳስ ፲፬ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23rd Year No. 7
ADDIS ABABA 23rd December, 2016

አዋጅ ቁጥር ፱፻፹፭/፪ሺ፰ ዓ.ም

የኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ.............ገጽ ፱ሺ፬፻፴፮

Proclamation No. 985/2016

Cooperative Societies Proclamation………...Page 9436

### አዋጅ ቁጥር ፱፻፹፭/፪ሺ፰ ዓ.ም

### ስለ ኅብረት ሥራ ማህበራት የወጣ አዋጅ

ተመሳሳይ ፍላጎት ባላቸው ሰዎች መካከል በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ኅብረት በመፍጠር ገንዘብን፣ ዕውቀትን፣ ንብረትንና ጉልበትን በማስተባበር የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊ፣ የባህላዊና ሌሎች የጋራ ፍላጎቶችን በማሟላት እርስ በርስ መደጋገፍንና ቁጠባን የሚፈጥሩ የኅብረት ሥራ ማህበራትን ማቋቋም እና መምራት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የኅብረት ሥራ ማህበራት በገጠር እና በከተማ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ፣ በአባላት ምርት ላይ ዕሴት በመጨመር፣ የግብይት እና የፋይናንስ ትስስር በመፍጠር፣ አላስፈላጊ የገበያ ሰንሰለትን በማሳጠር፣ በሃገር ውስጥ እና በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ በመሆን ለዜጎች የሥራ ዕድልን በመፍጠር በሀገሪቷ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ዕድገት ውስጥ የራሳቸውን አስተዋጽኦ ለማበርከት በአንድ ወጥ ሃገራዊ የኅብረት ሥራ ማህበር አዋጅ በመመራት በሕገ መንግስታችን አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ለመፍጠር የተቀመጠውን ዓላማ ለማሳካት ምቹ ሁኔታን መፍጠር በማስፈለጉ፤

፱ሺ፬፻፴፮

የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚከተሏቸውን መሠረታዊ መርሆዎችና ልዩ ባህሪ እንደጠበቁ በነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት ውስጥ ተገቢውን ሚና እንዲጫወቱ ማድረግ በማስፈለጉ፤

የአባላትን ባለቤትነት እና ተጠቃሚነት መብት

### PROCLAMATION No. 985/2016

### COOPERATIVE SOCIETIES PROCLAMATION

WHEREAS, it has become essential to establish and manage cooperative societies for those persons with common interest by bringing together their finance, knowledge, resource and labour voluntarily to meet their common economic, social and cultural needs and other aspirations which would then allow mutual support and create savings;

WHEREAS, cooperative societies are required to contribute to the country's economic and social development, and to be nationally and globally competent creation of an employment opportunities through supporting production and productivity increment in both rural and urban settings, value addition on members produce, creating financial and market linkage, shortening unnecessary market chains, in the way helpful to sustain one economic community in accordance to our constitution; through a uniform cooperative societies proclamation ;

የሚያረጋግጡ፣ አባላት የሚመሯቸውና የሚቆጣጠሯቸው ኅብረት ሥራ ማህበራትን ማደራጀት እና ማጠናከር በማስፈለጉ፤

የኅብረት ሥራ ማህበራትን ዓላማ ለማሳካት የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚደራጁበትንና የሚመሩበትን ሕግ በማውጣት በሥራ ላይ ያለውን የኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ መተካት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭ (፮) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፦

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ**

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር ፱፻፹፭/፪ሺ.፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡ –

፩/ "የኅብረት ሥራ ማህበር" ማለት ሰዎች ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊና ሌሎች የጋራ ፍላጎቶቻቸውን ለማሟላት እና በተናጠል ሊፈቱ ያልቻሏቸውን ችግሮች በጋራ ለማቃለል ተመሳሳይ ዓላማ ያላቸው ሰዎች በፈቃደኝነት የሚያቋቁሙት፣ በጋራ ባለቤት ነት የሚያስተዳድሩት፣ በኅብረት ሥራ ማህበራት መርህ መሠረት የሚመሩትና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የሚቆጣጠሩት ራሱን የቻለ ሕጋዊ ሰውነት ያለው የኅብረት ሥራ ማህበር ነው፤

፱ሺ.፬፻ ፴፰

፪/ "መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበር" ማለት የጋራ ፍላጎት እና ዓላማ ባላቸው ግለሰቦች በዚህ አዋጅ በተወሰነው አነስተኛው የአባላት መነሻ ቁጥር መሠረት ለማምረት፣ አገልግሎት ለማስጠት ወይም ሁለቱንም ለማከናወን የሚቋቋም የኅብረት ሥራ ማህበር ነው፤

፫/ "የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን" ማለት ተመሳሳይ ዓላማ ባላቸው መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት በዚህ አዋጅ በተወሰነው አነስተኛው የአባላት መነሻ ቁጥር መሠረት ከመሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት በላይ የሆነ የማምረት፣ አገልግሎት የማስጠት ወይም ሁለቱንም የማከናወን ተግባር ለመፈፀም የሚቋቋም

WHEREAS, it has become necessary to cause the cooperative societies to play pivotal role in the free market economic system by maintaining their guiding principles and unique features;

WHEREAS, it is necessary to establish and strengthen cooperative societies that are directed and managed by members and also ensure their rights, owners and benefits of them;

WHEREAS, it has become necessary to promulgate laws on establishment and management of cooperative societies by replacing existing cooperative societies proclamation, in order to achieve the objectives of the cooperative society;

NOW, THEREFORE, in accordance with the provisions of Ariticle 55 (6) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

**PART ONE**

**GENERAL**

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Cooperative Societies Proclamation No. 985/2016".

**2. Definitions**

In this Proclamation unless the context otherwise requires:

1/ "cooperative society" means an autonomous association having legal personality and democratically controlled by persons united voluntarily to meet their common economic, social and cultural needs and other aspirations, which could not addressed individually, through an enterprise jointly owned and operated on the basis cooperative principles;

ሁለተኛ ደረጃ የኅብረት ሥራ ማህበር ነው፤

፬/ "የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን" ማለት ተመሣሣይ ዓላማ ባላቸው የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዩኖች በዚህ አዋጅ በተወሰነው አነስተኛው የአባላት መነሻ ቁጥር መሠረት ከኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዩኖች በላይ የሆነ የማምረት፣ አገልግሎት የማስጠት ወይም ሁለቱንም የማከናወን ተግባር ለመፈፀም የሚቋቋም ሦስተኛ ደረጃ የኅብረት ሥራ ማህበር ነው፤

፭/ "የኅብረት ሥራ ማህበራት ሊግ" ማለት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዩኖች እና የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽኖችን የሚወክል ሊግ ነው፤

፮/ "ሁለገብ የኅብረት ሥራ ማህበር" ማለት ለአባላቱ የማምረት እና አገልግሎት የማስጠት ተግባራትን ለማከናወን የተቋቋመ የኅብረት ሥራ ማህበር ነው፤

፯/ "የቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማህበር" ማለት የቁጠባ፣ የብድር እና የብድር የሕይወት መድን አገልግሎቶችን ለአባላቱ ለማስጠት የተቋቋመ የኅብረት ሥራ ማህበር ነው፤

፱ሺ.፬፻ ፴፱

፰/ "የብድር የሕይወት መድን" ማለት ከኅብረት ሥራ ማህበር ብድር የወሰደ የኅብረት ሥራ ማህበር አባል ብድሩን ሙሉ በሙሉ ከፍሎ ሳይጨርስ በሞት ቢለይ ቀሪውን ብድር ለመክፈል የሚሰጥ የመድን ዋስትና ነው፤

፱/ "የኅብረት ሥራ ማኅበር የሥራ ክልል" ማለት በማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር መተዳደሪያ ደንብ የተወሰነና አግባብ ባለው ባለሥልጣን የተመዘገበ የሥራ ክልል ነው፤

፲/ "አባል" ማለት በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት እንደኅብረት ሥራ ማህበሩ አይነት የተደነገጉትን የአባልነት መመዘኛዎችን በማሟላት ለአባልነት ጥያቄ አቅርቦ ተቀባይነት ያገኘ ግለሰብ ወይም መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር ወይም የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዩን ወይም የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን ነው፤

፲፩/ "ጠቅላላ ጉባኤ" ማለት የአንድ መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማኅበር ግለሰብ አባላት ወይም ተወካዮቻቸው ወይም ከመሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበር በላይ ከሆነ የመሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት፣

2/ "primary cooperative society" means a cooperative society established by individuals having similar interest and objective with a minimum number of members prescribed in this Proclamation to produce, provide service or to engage in both activities;

3/ "cooperative societies union" means a secondary level cooperative society established by primary cooperative societies having similar objective with a minimum number of members as prescribed in this Proclamation to produce, provide service or to engage in both activities that are beyond the capacity of primary cooperative societies;

4/ "cooperative societies federation" means a tertiary level cooperative society established by cooperative society unions having similar objective with a minimum number of members prescribed in this Proclamation, to produce, provide service or to engage in both activities that are beyond the capacity of cooperative society unions;

5/ "cooperative societies league" means a league which represents primary cooperative societies, cooperative society unions and cooperative society federations operating in Ethiopia;

6/ "multi-purpose cooperative society" means a society established to engage in production and service delivery activities for its members;

7/ "saving and credit cooperative society" means a society established to provide saving, credit and loan-life-insurance services to its members;

የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒየኖች ወይም የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽኖች ተወካዮች የሚገኙበት ጉባኤ ነው፤

፲፪/ "ተወካይ" ማለት አወካከሉ በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ በሚወሰነው መሠረት ሆኖ በመሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበር በግለሰብ አባላት ተወክሎ በጠቅላላ ጉባኤ ድምጽ የሚሰጥ ወይም በኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዩን ወይም በኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን በጠቅላላ ጉባኤ ተመርጦ የኅብረት ሥራ ማህበራትን ተክቶ በማንኛ ውም የኅብረት ሥራ ማህበር ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ላይ በመገኘት ድምፅ የሚሰጥ ግለሰብ ነው፤

፲፫/ "መተዳደሪያ ደንብ" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፪ የተመለከቱትን ዝርዝሮች አሟልቶ የያዘ፣ አግባብ ባለው አካል የተመዘገበ እና በየጊዜው የሚሻሻለውንም ጨምሮ በኅብረት ሥራ ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ በሁለት ሦስተኛ ድምፅ የፀደቀ የኅብረት ሥራ

፱ሺ፬፻፴፱ ማህበሩ የሚተዳደርበት ሕግ ነው፤

፲፬ "ልዩ ውሳኔ" ማለት በአባላቱ ላይ አስገዳጅነት እንዲኖረው በኅብረት ሥራ ማህበሩ አባላት በሁለት ሦስተኛው ድምጽ መጽደቅ ያለበት ውሣኔ ነው፤

፲፭/ "የሥራ አመራር ኮሚቴ" ማለት በጠቅላላ ጉባኤ ተመርጦ የአንድን የኅብረት ሥራ ማህበር ሥራዎችን እንዲመራ ኃላፊነት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፮/ "ሥራ አስኪያጅ" ማለት ለኅብረት ሥራ ማህበር ሥራ አመራር ኮሚቴ ተጠሪ የሆነና በተሰጠው ኃላፊነትና ሥልጣን ገደብ መሰረት የኅብረት ሥራ ማህበሩን የዕለት ተዕለት ሥራዎችን የሚያንቀሳቅስ የሥራ ኃላፊ ነው፤

፲፯/ "ሠራተኛ" ማለት ከአሰሪው የኅብረት ሥራ ማህበር ጋር በገባው ውል መሠረት የዕለት ተዕለት ሥራዎችን እንዲያካሄድ በቅጥር ላይ የተመሰረተ የሥራ ግንኙነት ያለው ግለሰብ ነው፤

፲፰/ "የመጠባበቂያ ሐሳብ" ማለት የኅብረት ሥራ ማህበሩ ከዓመታዊ ትርፉ በሕጉ መሰረት ለመጠባበቂያነት የሚያስቀምጠውና ለአባላት በትርፍ ድርሻነት የማይከፋፈለው ሂሳብ ነው፤

፲፱/ "ካፒታል" ማለት የኅብረት ሥራ ማህበር ካለው ጠቅላላ ሀብት ላይ ዕዳው ተቀንሶ የሚቀረው የሀብት መጠን ሲሆን የአባላትን የዕጣ ሽያጭ፣ የመጠባበቂያ ሂሳብ፣ ስጦታ፣ ወርስ እና በመተዳደሪያ ደንቡ

8/ "loan-life-insurance" means an insurance given by a cooperative society to its members to cover loan taken by a deceased member before full repayment of debt;

9/ "cooperative's societies working area" means an area stated in cooperative society's by-laws and registered by appropriate authorities;

10/ "member" means any individual or a primary cooperative society or a cooperative societies union or cooperative societies federation who applied and admitted for membership upon fulfilling the minimum membership requirements that are determined in the by laws by taking into account the nature of the cooperative society;

11/ "General Assembly" means a meeting of individual members or their representatives at primary cooperative society or representatives of primary cooperative societies, cooperative societies unions or cooperative societies federations when it is above primary cooperative society;

12/ "representative" means as prescribed in the by-law of the cooperative society with regards representation, an individual in primary cooperative societies, represented by members to vote in general assembly, or in cooperative unions and federations elected by General Assembly of the cooperative society to represent and vote for in any General Assembly of the cooperative society;

13/ "by-laws" means the law governing a cooperative society including amendments made to it and approved by two third vote of the General Assembly and registered by appropriate body upon fulfilling particulars specified under Article 12 of this Proclamation;

የሚወሰኑ ፈንዶች እና ኢንቨስትመንቶችን የያዘ ነው፤

፳/ "አግባብ ያለዉ ባለስልጣን" ማለት የፌደራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ ወይም በክልል የኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅን ለማስ ፈጸም፣ ዘርፉን ለመምራት እና ለመቆጣጠር የተቋቋመ አካል ነው፤



፳፩/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፵፯ (፩) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና የድሬዳዋ አስተዳደርን ይጨምራል፤

፳፪/ "የኅብረት ስራ ማህበራት ፈንድ" ማለት ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ለተለያዩ የጋራ ጥቅሞች ለትምህርት ወይም ለስልጠና ወይም ለኦዲት አገልግሎት ወይም ለማበ ረታቻ ወይም ለጥናት እና ምርምር ወይም ለህግ አገልግሎት ወይም ለፕሮሞሽንና ኮሚኒኬሽን እና ለማህበራዊ አገልግሎት የሚያወላቸውን ከኅብረት ስራ ማህበራት ዓመታዊ የተጣራ ትርፍ በጠቅላላ ጉባዔ ሲወሰን የሚገኝ ገቢ እንዲሁም የኅብረት ስራ ማህበራት ከስጦታ ወይም ከወርስ ወይም የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በመሥራት ከዕርዳታ እና ከተለያዩ ገቢ ማስገኛዎች የተገኙ ገቢዎችን እና የኅብረት ስራ ማህበራት ህልወናቸውን በሚያጠፉበት ጊዜ የማይከፋ ፈሉት የጋራ ገንዘብና ንብረት የሚሰባሰብበት ፈንድ ነው፤

፳፫/ "የዕጣ ክፍያ" ማለት በኅብረት ስራ ማህበሩ የታወጀ ዋጋ ያለው እና ለአባልነት እንደ መጀመሪያ ቅድመ ሁኔታ በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት የተሸጠ ወይም የሚሸጥ ነው፤

፳፬/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፳፭/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ያካትታል፡፡

## ፫. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ በመላ ሀገሪቱ ወስጥ በሚደራጁ የኅብረት ሥራ ማህበራት ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

## ፬. የኅብረት ሥራ ማህበር ዓላማዎች

በዚህ አዋጅ መሠረት የሚቋቋም ኅብረት ሥራ ማህበር

14/ "special resolution" means a resolution passed by a two third majority of the members of the cooperative society to be binding on all members;

15/ "management committee" means a body elected and empowered by the general assembly with the responsibility to manage the activities of a cooperative society;

16/ "manager" means an officer accountable to the management committee and operates the day-to-day activities of the cooperative society within the limit of the powers and responsibilities entrusted to it;

17/ "worker" means an individual who has an employment relationship with the employer cooperative society to perform day-to-day activities in accordance with the agreement reached in the contract of employment;

18/ "reserve fund'' means part of annual surplus retained and reserved by cooperative societies in accordance with the law and not distributed as dividend to members;

19/ "capital" means the amount of asset accumulated after deducting liability of a cooperative society, and it includes share of the members, reserve fund, donation, inheritance, and funds prescribed by by-laws and investments;

20/ "appropriate authority" means the Federal Cooperative Agency, or an organ established at regional levels to execute the cooperative societies proclamation, lead and regulate the cooperative sector;

የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩/ አባላት በተናጠል በመሥራት ሊወጧቸው የማይችሏቸውን የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ችግሮችን በተባበረ ጥረት

፱ሺ፬፻፵፪ ሠወጣት፣ መቋቋም እና መፍታት፤

፪/ አባላት ያላቸውን ዕውቀት፣ ሀብትና ጉልበት በማቀናጀት የተሻለ ወጤት ማግኘት፤

፫/ በአባላት ዘንድ በራስ መተማመን ማጎልበት፤

፬/ ለማምረት የሚያስፈልገውን ወጪ የአገል ግሎት ዋጋን በመቀነስ አባላት የሚፈልጉትን ግብአት ወይም አገልግሎት በአነስተኛ ዋጋ እንዲያገኙ ማድረግ እና ምርታቸው ወይም አገልግሎታቸው የተሻለ የገበያ ዋጋ እንዲያገኝ ማስቻል፤

፭/ የቴክኒክ ዕውቀትን እና የሥራ ፈጠራን በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች እንዲ ስፋፉ ማድረግ፤

፮/ በአባላት መካከል የቁጠባ ባህል እንዲዳብር እና እንዲስፋፋ ማድረግ፤

፯/ ለአባላት የብድር አገልግሎትን በማስጠት ኢንቨስትመንትን ማስፋፋት፤

፰/ ለአባላት የብድር የሕይወት መድን ዋስትና ማስጠት፤

፱/ አባላቱ በግላቸው ቢሰሩ ኖሮ ሊደርስባቸው የሚችለውን ጉዳትና ኪሣራ በጋራ በማካፈል የእያንዳንዱን ሰው ጉዳትና ኪሣራ መቀነስ፤

፲/ አባላትን በማስተማርና በማሰልጠን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ አቅማቸውንና ባህላቸውን ማጎልበት፡፡

## ፭. የኅብረት ሥራ ማህበራት መሠረታዊ መርሆዎች

፩/ የኅብረት ሥራ ማኅበራት አባልነት በማኅ በራቱ አገልግሎት ለመጠቀም ለሚፈልጉና የአባልነት ግዴታዎችን ለመቀበል ፈቃደኛ ለሆኑ ሰዎች ሁሉ በጾታ፣ በማኅበራዊ አቋም፣ በዘር፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ በአካል ጉዳተኝነት ወይም በሃይማኖት ልዩነት ሳይደረግ ለሁሉም ክፍት ይሆናል፡፡

፪/ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ፖሊሲ በማውጣ ትና ወሳኔዎችን በማስተላለፍ የነቃ ተሳትፎ በሚያደርጉ አባላት የሚመሩ ዲሞክራሲያዊ ድርጅቶች፣ እያንዳንዱ አባል እኩል ድምጽ ያለው እንዲሁም አንድ አባል አንድ ድምጽ ብቻ ያለው ይሆናል፡፡

፱ሺ፬፻፵፫

፫/ ከትርፍ ላይ ለመጠባበቂያ እና ለሌሎች አገልግሎቶች ተቀንሶ ከተቀማጠ በኋላ አባላት ከኅብረት ሥራ ማህበሩ በገዙት ዕጣ ማጠን እና ባደረጉት ተሣትፎ መሠረት ቀሪው ትርፍ ይከፋፈላል፡፡

21/ "region" means any state referred to in Article 47 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the Addis Ababa City Admin istration and Dire Dawa Administration;

22/ "copoperative societies fund" means a type of fund established to achieve copperative societies jont benefit for education or training or audit service or incentive, or research and development or legal service or for promotion and communication, and for social services purpose by pulling incomes from cooperatives net income as decided after audit by the general assembly, and also income from gift or hire or different project initiatives or support and income from different income generating activities and other incomes pulled from common indivisible money and asset remained after the liquidation of cooperative societies;

23/ "Payment of shares" means the declared share having par value and serve members as precondition for membership paid prescribed in cash or in kind;

24/ "person" means a natural or juridical person;

25/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

## 3. Scope of application

This proclamation shall apply to cooperative societies established in the country.

## 4. Objectives of a Cooperative Society

A cooperative society established pursuant to this Proclamation shall have any one or more of the following objectives:

1/ to collectively overcome, withstand and solve economic and social problems which members cannot individually achieve;

፯/ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ከሌሎች አካላት ጋር መንግሥትንም ጨምሮ ስምምነት የሚያደርጉት ወይም ከኅብረት ሥራ ማኅበራቸው ውጭ ከሚገኝ ምንጭ ገንዘብ በማበደር ካፒታላቸውን ማሳደግ የሚችሉት የአባላትን ዲሞክራሲያዊ ቁጥጥር በሚያረጋግጥ፣ የኅብረት ሥራ ማኅበራቸውን የራስ በራስ ማስተዳደር መብት በሚጠብቅ እንዲሁም የራስ አገዝ ባህሪውን በማይነካ ሁኔታ መሆን ይኖርበታል፡፡

፰/ የኅብረት ሥራ ማኅበራት አባላት፣ ተመራጮች፣ ሥራ አስኪያጅ እና ሠራተኞች ለኅብረት ሥራ ማኅበራቸው ዕድገት ተገቢውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ትምህርትና ሥልጠና እንዲያገኙ ያደርጋሉ፤ ስለ ኅብረት ሥራ ማኅበራት ምንነትና ጥቅም ለሕዝቡ በተለይም ለወጣቱ ያስተዋውቃሉ፡፡

፱/ በአካባቢ፣ በሀገር አቀፍ፣ በአህጉር አቀፍ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሚገኙ የኅብረት ሥራ ማህበራት መዋቅሮች ጋር በመተባበር የኅብረት ሥራ ማህበራት እንቅስቃሴን በማጠናከር አባሎቻቸውን በሚገባ ያገለግላሉ፡፡

፲/ የኅብረት ሥራ ማኅበር አባሎቹ ባፀደቋቸው ፖሊሲዎች አማካኝነት በአካባቢያቸው ላለው ኅብረተሰብ ዘላቂ ልማት ለማምጣት የሚያስችል ተግባር ያከናወናሉ፡፡

## ፭. <u>የኅብረት ሥራ ማህበራት እና የአባላት እሴቶች</u>

፩/ የኅብረት ሥራ ማህበራት እሴቶች የሚከተሉት ይሆናሉ፦
ሀ) ራስን በራስ መርዳት፤
ለ) የግል ሃላፊነትን መወጣት፤
ሐ) የዴሞክራሲ ባህልን ማስፋፋት፤
መ) እኩልነት፤
ሠ) ፍትሃዊነት፤
፱ሺ፬፻፵፬ ረ) ወንድማማችነት፡፡

፪/ የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት የሥነ-ምግባር እሴቶች የሚከተሉት ይሆናሉ፦
ሀ) ታማኝነት፤
ለ) ግልፀኝነት፤
ሐ) ተጠያቂነት፤
መ) አሳታፊነት፤
ሠ) ማህበራዊ ኃላፊነት፤ እና
ረ) ለሌሎች ማሰብ፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

2/ to achieve a better result by coordinating members' knowledge, resource and labor;

3/ to promote self-reliance among members;

4/ to reduce production and service costs and to offer inputs and services to members with lower costs and finding better market prices to their products or services;

5/ to expand situations by which technical knowledge could be put into practice and promote entrepreneurship;

6/ to develop and promote saving culture between members;

7/ to provide loan to members and promote investment;

8/ to provide loan-life- insurance coverage to members;

9/ to minimize and reduce damage and lose of each individual members, if it had been undertaken individually, by sharing it to members;

10/ to develop the social and economic capacity and culture of the members through education and training.

## 5. Guiding Principles of Cooperative Societies

1/ Cooperative societies shall be voluntary organizations open to all persons willing to use their services and able to accept the responsibilities of membership without discrimination on the basis of gender, social status, race, political ideology, disability or religion.

2/ Cooperative societies shall be democratic organizations controlled by their members who actively participate in setting their policies and making decisions; each member having equal voting right as well as one member having only one vote.

## ስለኅብረት ሥራ ማኅበራት አመሠራረትና ምዝገባ

### ፮. ስለኅብረት ሥራ ማህበራት አመሠራረት

፩/ የኅብረት ሥራ ማህበራት እንደየባህሪያቸው ከመ ሠረታዊ እስከ ፌዴሬሽን በየደረጃው ሊማሰረቱ ይችላሉ፡፡

፪/ የመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበር፦

ሀ) በተወሰነ አካባቢ በሚኖሩ ወይም በሚሠሩ ወይም በተወሰነ ሙያ በተሰማሩ ግለሰቦች፤ እና

ለ) ቁጥራቸው ከሃምሣ በማያንሱ አባላት፤

ይደራጃል፡፡

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ፊደል ተራ (ለ) ቢኖርም የሥራ ባህሪያቸውን እና የኢኮኖሚያዊ አዋጭነታቸውን መሠረት በማድረግ አግባብ ያለው ባለሥልጣን የማነሻ ቁጥርን በመመሪያ ሊወስን ይችላል፤ ሆኖም የማነሻ ቁጥሩ ከ፲ ሊያንስ አይችልም፡፡

፬/ በፌደራል ደረጃ የሚደራጅ መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር አባላት ነዋሪነታቸው ከሁለት እና ከዚያ በላይ ከሆኑ ክልሎች የተውጣጡ ግለሰቦች መሆን አለባቸው፡፡

፭/ አግባብ ያለው ባለሥልጣን የኅብረት ሥራ ማህበራትን በፌደራል ወይም በክልል ደረጃ በማደራጀት የሚመዘግብ ይሆናል፡፡

### ፯. የኅብረት ሥራ ማኅበራት ዓይነቶች

፩/ የኅብረት ሥራ ማህበር ምርት የማምረት ወይም አገልግሎት የማስጠት ወይም ምርት የማምረት እና አገልግሎት የማስጠት ሁለገብ ተግባር አጣምሮ የሚያከናውን ሆኖ ሊመሠረት ይችላል፡፡

፱ሺ፬፻፵፫

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለኅብረት ስራ ማህበራት በህግ በተከለከሉ የህዝብን ሞራላዊ እሴቶች በሚነኩ፣ የአካባቢን ደህንነት በሚጎዱ ተግባራት መደራጀት የማይቻል ሲሆን አግባብ ባለው ባለስልጣን የኢኮኖሚ አዋጭነት እንዲሁም በሚደራጁበት አካባቢ ሀብት መኖሩን በጥናት በማየት የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚደራጁባቸውን የአማራጭ ዓይነቶች በማቅረብ ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

### ፰. የኅብረት ሥራ ማኅበር ስም

፩/ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማኅበር ማጠሪያ ስም ይኖረዋል፣ የስም አወጣጡም ምክንያታዊ፣ ሕግንና የሕዝብን ሞራል የማይቃረን መሆን አለበት፡፡

፪/ ከማንኛውም የኅብረት ሥራ ማኅበር ስም ማጬረሻ

3/ Members shall receive dividends from surplus according to their shares and participation after deducting and setting aside an amount necessary for reserve and other services.

4/ Cooperative societies shall, when enter into agreement with other organizations including government or raise capital from external sources, do so on terms that ensure democratic control by their members, maintain their autonomy and do not affect their self-help characteristics.

5/ Cooperative societies shall provide education and training for their members, elected representatives, managers and employees so as to enable them to contribute effectively to the development of their societies and, advertize to the public at large particularly to the youth about the nature and benefit of societies.

6/ Cooperative societies shall serve their members most effectively and strengthen the cooperative movement by working together through local, national, regional and international structures.

7/ Cooperative society shall work for the sustainable development of their community through policies approved by their members.

### 6. Values of the Cooperative Societies and their Members

1/ The values of the cooperative societies shall be:

a) self-help;

b) self-responsibility;

c) promoting culture of democracy;

d) equality;

e) equity; and

f) Solidarity.

"ኃላፊነቱ የተወሰነ የኅብረት ሥራ ማኅበር" የሚል ሐረግ መጻፍ ይኖርበታል፡፡

፫/ አንድ የኅብረት ሥራ ማኅበር በተመዘገበበት ስም፣ ማለያ ምልክት እና የሥራ ክልል ውስጥ ሌላ የኅብረት ሥራ ማኅበር ተመሳሳይ እና አሳሳች ስም ወይም ማለያ ምልክት መጠቀም አይችልም፡፡

፬/ የማንኛውም የኅብረት ሥራ ማኅበር ስም ጉልህ ሆኖ ተጽፎ የኅብረት ሥራ ማኅበሩ ሥራ በሚከሄድበት በማንኛውም ሥፍራ መለጠፍ አለበት፡፡ እንዲሁም በኅብረት ሥራ ማኅበሩ ማስታወቂያዎች፣ ደብዳቤዎች፣ ሌሎች መግለጫ ዎችና በኅብረት ሥራ ማኅበሩ ስም በሚፈረሙ ሰነዶች ላይ መጻፍ ወይም ማኅተም መደረግ አለበት፡፡

፭/ ማንኛውም ሰው አግባብ ካለው ባለሥልጣን ፈቃድ ሳያገኝ "የኅብረት ሥራ ማኅበር" የሚለውን ስያሜ መጠቀም አይችልም፡፡

## ፮. ስለ ኅብረት ሥራ ማኅበር ምዝገባ

፩/ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማኅበር አግባብ ባለው ባለሥልጣን መመዝገብ አለበት፡፡

፪/ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማኅበር፣ የኅብረት ሥራ ማኅበር ሆኖ ለመመዝገብ ማመልከቻውን ከሚከተሉት ጋር

፱ሺ፬፻፵፬ ያይዞ አግባብ ላለው ባለሥልጣን ያቀርባል፡-

ሀ) የመሥራቾች ስብሰባ ቃለ ጉባኤ፤

ለ) የኅብረት ሥራ ማኅበሩን መተዳደሪያ ደንብ ሦስት ቅጂዎች፤

ሐ) የኅብረት ሥራ ማኅበሩን የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት ስም፣ አድራሻና ፊርማ፤

መ) የኅብረት ሥራ ማኅበሩን የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት ስም፣ አድራሻና ፊርማ፤

ሠ) የኅብረት ሥራ ማኅበር አባላት ሆነው የሚመዘገቡት ግለሰቦች በዚህ አዋጅና በኅብረት ሥራ ማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ በተወሰነው መሠረት አባል ለመሆን ብቁ መሆናቸውን የሚያስረዱ ዝርዝር መግለ ጫዎች፤

ረ) የኅብረት ሥራ ማኅበሩ ከመሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማኅበር በላይ ከሆነ የአባል ኅብረት ሥራ ማኅበራትን አድራሻ እና የተወካዮች ፊርማ፤

ሰ) ከሶስት እስከ አምስት ዓመት የሚደርስ የኅብረት

2/ The ethical values of the members of the cooperative societies shall be:

a) honesty;

b) openness;

c) accountability;

d) participatory ;

e) social responsibility; and

f) caring for others.

## PART TWO

## FORMATION AND REGISTRATION OF COOPERATIVE SOCIETIES

### 7. Formation of Cooperative Societies

1/ Cooperative societies may, according to their nature, be established at different levels from primary up to federation level.

2/ The primary cooperative society shall be established:

a) by individuals who live or work or engaged in specific profession within a given area; and

b) by number of members not less than fifty.

3/ Notwithstanding paragraph (b) of sub-article (2) of this Article, the appropriate authority may specify in the directive the minimum number of members of a society based on the nature of the work and economic feasibility; provided, however, that the minimum number of members shall not be less than 10.

4/ Primary cooperative society established at federal level shall consist members from two or more regional states.

5/ The appropriate authority shall establish and register cooperative societies at federal or regional levels.

### 8. Type of Cooperative Societies

1/ A cooperative society may be established to engage in production or service rendering activities or both in production and service rendering activities.

ሥራ ማህበሩ የስራ እቅድ ሰነድ፤

ሸ) የመነሻ ካፒታሉን መጠንና ተሰብስቦ በባንክ ሂሳብ ገቢ መደረጉን ወይም ባንክ በሌለበት አካባቢ ከሆነ መዝጋቢው በወሰነው የፋይናንስ ተቋም መቀመጡን የሚያረጋግጥ ሰነድ፤

ቀ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሚሠራበት ቦታ መገለጫ

በ) ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች የሚወሰኑ ሌሎች መግለጫዎች፡፡

፫/ አግባብ ያለው ባለሥልጣን የቀረበለትን የምዝገባ ማመልከቻ መርምሮ የተሟላ መሆኑን ሲያረጋግጥ በአምስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ የኅብረት ሥራ ማህበሩን መዝግቦ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡ በዚህም የምዝገባ ምስክር ወረቀት ላይ የኅብረት ሥራ ማህበሩ በኅብረት ሥራ ማህበርነት
፱ሺ፬፻፵፭ ተመዝገበበት ቀን ይጠቀሳል፡፡

፬/ አግባብ ያለው ባለሥልጣን አመልካቹን የኅብረት ሥራ ማህበር መመዝገብ አይገባውም ሲል የወሰነ እንደ ሆነ ምክንያቱን በጽሑፍ በማድረግ ለኅብረት ሥራ ማህበሩ ወኪሎች ካማለከቱበት ቀን ጀምሮ በአምስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ መግለፅ አለበት፡፡

፭/ የአመልካች ወኪሎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት በጽሑፍ በተሰጠው ወሳኔ ላይ ቅሬታ ያላቸው ከሆነ፣ በክልል ሲሆን አግባብ ላለው የክልሉ ፍርድ ቤት ወይም በፌደራል ደረጃ ሲሆን ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በ፴ ተከታታይ ቀናት ውስጥ አቤቱታ ማቅረብ ይችላሉ፡፡

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የተሰጠ የምዝገባ የምስክር ወረቀት የኅብረት ሥራ ማህበሩ በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት የተመዘገበ ለመሆኑ በቂ ማስረጃ ይሆናል፡፡

፯/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት በሕጋዊ መንገድ የተመዘገበ ማንኛወም የኅብረት ሥራ ማህበር በተመዘገበበት ዓላማና በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ ለተፈቀደለት የሥራ መስክ ሌላ ተጨማሪ የንግድ ፈቃድ ሳያስፈልገው ይሠራል፡፡

፰/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (፪) (ሀ) እስከ (ሸ) የተዘረዘሩት ማስፈርቶች የተሟሉ መሆኑን አግባብ ያለው ባለሥልጣን ሲያረግጥ ከአንድ አመት ላልበለጠ ጊዜ የሚያገለግል ጊዜያዊ የምስክር ወረቀት

2/ Without the prejudice to the provision of sub-article (1) of this Article, types of cooperative societies to be established shall not in the areas prohibited by law, immoral to public values, activities affecting environmental security, hence the appropriate authority shall give professinoal support after conducting due socio-economic study in order to identify the potential resources a vairable to organize cooperative societies.

## 9. Name of a cooperative Society

1/ Any cooperative society shall have its own name; and such name shall be rational, does not contravene law and public morality.

2/ The phrase "Cooperative Society with Limited Liability" shall appear in the end of the name of any cooperative society.

3/ No similar and misleading name or distinguishing mark shall be used by another cooperative society within the same operation area of a registered name or distinguishing mark of a given cooperative society.

4/ The name of any cooperative society shall be written boldly and be put at every place where the cooperative society's activities are performed. It shall also be written or sealed on any notices, letters, other statements and documents which are signed on behalf of the cooperative society.

5/ No person may use the name "Cooperative Society" without obtaining permission from the appropriate authority.

## 10. Registration of a cooperative society

1/ Any cooperative society shall be registered by the appropriate authority.

2/ Any cooperative society, to get registered as a cooperative society, shall submit an application for registration together with the following particulars to the appropriate authority:

ሰጥቶ የተቀሩት ማስፈርቶች በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲሟሉ ማስደረግ ይችላል፡፡

፱/ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ከተቋቋ ማባት ዓላማና ሮሀ ውጪ ሲንቀሳቀስ ከተገኘ በዚህ ሕግ የተፈቀደለትን ሥራ እንዳይሠራ አግባብ ያለው ባለሥልጣን ሊያግደው ይችላል፡፡



፲/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፱) መሠረት የታገደው የኅብረት ሥራ ማህበር ዕግዱ እንዲነሳለት በ፴ ተከታታይ ቀናት ውስጥ ካላማለከተ አግባብ ያለው ባለሥልጣን ሕጋዊ የማፍረስ እርምጃ ይወስዳል፡፡

፲፩/በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፱) መሠረት የታገደ የኅብረት ስራ ማህበር ጠቅላላ ጉባኤ ዕግዱ እንዲነሳለት አግባብ ላለው ባለሥልጣን ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ ጥያቄውን የተቀበለው አግባብ ያለው ባለሥልጣን የኅብረት ሥራ ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ እግዱ እንዲነሳለት ያቀረበው ምክንያት በቂና አግባብ ሆኖ ሲያገኘው እግዱን ሊያነሳ ይችላል፡፡ አግባብ ያለው ባለሥልጣን እግዱን ያላነሳ እንደሆነ ያላነሳበትን ምክንያት በጽሑፍ ያሳውቃል፡፡ አግባብ ያለው ባለሥልጣን በሰጠው ወሳኔ ያልተስማማ አካል ዕግዱ የተሰጠው በፌደራል ደረጃ ከሆነ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም ዕግዱ በክልል ደረጃ ከሆነ ስልጣን ላለው ለክልሉ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

## ፲፩. የሕግ ሰውነትና ኃላፊነት

፩/ ማንኛወም የኅብረት ሥራ ማነበር በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲ መሠረት ከተማዝገበበት ቀን ጀምሮ በሕግ የሰውነት መብት ይኖረዋል፡፡

፪/ ማንኛወም የኅብረት ሥራ ማህበር ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፤ ኃላፊነቱ የተወሰነ ነው፡፡

## ፲፪. የኅብረት ሥራ ማነበር መተዳዳሪያ ደንብ

፩/ ማንኛወም የኅብረት ሥራ ማህበር መተዳደሪያ ደንብ ይኖረዋል፣ የመተዳደሪያ ደንቡ ይዘት የሚከተሉትን ይጨምራል፡−

ሀ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን ስምና አድራሻ፤

ለ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን ዓላማና ተግባር፤

ሐ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን የሥራ ቦታ እና

a) minutes of the founders meeting;

b) the by-laws of the cooperative society in three copies;

c) names, address and signature of the members of the management committee of the cooperative society;

d) name, address and signature of the members of the control committee of the cooperative society;

e) a detailed description which proves that the registered members of the cooperative society have met the requirements for membership in accordance with the provisions of this Proclamation and the by-laws of the cooperative society;

f) if the cooperative society is of a higher level than the primary cooperative society, the name and address of the member primary cooperative societies and signature of their representatives;

g) three up to five years action plan of the society;

h) documents showing the amount of initial capital of the society and the capital that has been collected and deposited in a bank account, if there is no bank in the area, that it has been deposited in a Financial Institution where the appropriate authority has designated;

i) the description of the place at which the cooperative society operates;

j) other particulars that may be specified in the regulations or directives issued hereunder;

3/ The appropriate authority shall register the cooperative society and issue a certificate of registration within five consecutive working days when it is satisfied that the application for registration submitted to it has fulfilled the requirements for registration. The date of registration of the cooperative society as a cooperative society shall be recorded on the certificate of registration.

አካባቢ፤

መ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ አባል ለመሆን የሚያበቁ መመዘኛዎችን፤

ሠ) ስለኅብረት ሥራ ማህበሩ አባላት መብትና ግዴታዎች፤

ረ) ስለ ኅብረት ሥራ ማህበሩ አመራር አካላት ሥልጣን፣ ኃላፊነትና ተግባር፤

ሰ) አባላት ከኅብረት ሥራ ማኅበሩ ስለሚወጡበትና ስለሚሰናበቱበት ሁኔታ፤

ሸ) ስለ ኅብረት ሥራ ማህበሩ ሥራ አመራር ኮሚቴ አባላትና ሌሎች የሥራ ኃላፊዎች ምርጫ፣ ሹመትና የሥራ ጊዜ እንዲሁም ከኃላፊነት ስለሚታገዱበት ወይም ስለሚ ሰናበቱበት ሁኔታ፤

ቀ) ስለ ኅብረት ሥራ ማህበሩ ስብሰባ አጠራር እና ስለድምጽ አሰጣጥ፤

በ) ስለትርፍ አመዳደብና ክፍፍል፤

ተ) ስለሂሣብ ምርመራ፤

ቸ) ስለሠራተኛ አቀጣጠር፤

ኀ) ይህን አዋጅ እና በዚህ አዋጅ ማሰረት የሚወጣ ደንብ እና መመሪያን የማይ ቃረኑ ሌሎች ጉዳዮች፡፡

፪/ የኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳዳሪያ ደንብ በጠቅላላ ጉባዔው ልዩ ውሣኔ ሊሻሻል ይችላል፤ ሆኖም የማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር መተዳዳሪያ ደንብ ማሻሻያ ሊጸና የሚችለው አግባብ ላለው ባለሥልጣን ቀርቦ ከተመዘገበበት ቀን አንስቶ ይሆናል፡፡

፫/ የማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር የመተዳደሪያ ደንብ እንዲሻሻል በጠቅላላ ጉባዔው ሲወሰን የተደረገው ማሻሻያ እና በዚህ አዋጅ መሠረት የተላላፈ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ወሳኔ በሦስት ቅጅ ተደርጎ ወሳኔ በተላለፈ በ፲፭ ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ አግባብ ላለው ባለሥልጣን መቅረብ አለበት፡፡ የመተዳደሪያ ደንቡ ማሻሻያ በተጠቀሰው ቀን ወስጥ አግባብ ላለው ባለሥልጣን ካልቀረበ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የቀረበው የመተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያ ይህንን አዋጅና አዋጁን ለማስፈጸም የወጣውን ደንብ እና መመሪያ የማይቃረን መሆኑን አግባብ ያለው ባለሥልጣን ሲያረጋግጥ

4/ When the appropriate authority rejects the application for the registration of a cooperative society, it shall give a written explanation to the representatives of the cooperative society starting from the date of application within five consecutive working days.

5/ If representatives of the cooperative society have grievance on the written decision of the appropriate authority given pursuant to sub-article (4) of this Article, they may lodge petition, to the appropriate Regional Court, if it is at regional level and to the Federal High Court, if it is at federal level, within 60 consecutive days to high court which has jurisdiction.

6/ The certificate of registration issued to a cooperative society pursuant to sub-article (3) of this Article shall be a sufficient evidence to prove that a cooperative society is registered in accordance with this Proclamation.

7/ Any cooperative society which has been legally registered pursuant to sub -article (3) of this Article shall engage in business in accordance with its objectives and activities endorsed in its by-law as of the date of registration without the need to secure additional business license.

8/ Where the appropriate authority ensures that requirements indicated under paragraph (a) to (h) of sub-article of this Article are met, it shall grant temporary certificate which may serve not more than a year and shall cause the rest requirements to be observed within a specified period of time.

9/ Where any cooperative society is found operating out of the objectives and principles for which it is established, the appropriate authority may suspend it from carrying out activities permitted by this law.

ማሻሻያውን ይመዘግባል፤ የምዝገባ ማስረጃውንም በአምስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ይሰጣል፡፡

፲/ አግባብ ያለው ባለሥልጣን የመተዳደሪያ ደንቡን ማሻሻያ ካልመዘገበ ወይም የማይመዘግብበትን ምክንያት በአምስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ለኅብረት ሥራ ማህበሩ ካላሳወቀ የተሻሻለው መተዳደሪያ ደንብ እንደተመዘገበ ተቆጥሮ በሥራ ላይ ይውላል፡

፲፩/ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ የኅብረት ሥራ ማኅበሩን መርሆዎች እና እሴቶች ማካተት አለበት፡፡

፲፪/ ማንኛውም የኅብረት ስራ ማህበር በማህበሩ የአመራር አካላት አባልነት ውስጥ የሴቶችን ተሣትፎ ለማሣደግና ለማበረታታት የሚያስችል ማስፈርት ማካተት አለበት፡፡

፲፫/ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር የሴቶችን፣ የወጣቶችን እና የአካል ጉዳተኞችን ተሳትፎ የሚያሳድጉ ተግባራትን በስትራቴጂክ እና በዓመታዊ እቅዶቹ ውስጥ ማካተት አለበት።

## ፲፫. ስለኅብረት ሥራ ማኅበራት ውህደትና መከፋፈል

፩/ የኅብረት ሥራ ማህበር ጠቅላላ ጉባዔ በልዩ ውሣኔ፡-

ሀ) ራሱን በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ የኅብረት ሥራ ማህበራት ሊከፋፍል፤ ወይም

ለ) ከአንድ ወይም ከዚያ በላይ ከሆኑ ኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር በመዋሃድ አዲስ የኅብረት ሥራ ማኅበር ሊመሠርት፤

ይችላል፡፡

፪/ የኅብረት ሥራ ማኅበር መዋሃድ ወይም መከፋፈል ልዩ ውሣኔ ተፈፃሚ የሚሆነው፡-

ሀ) የኅብረት ሥራ ማኅበሩ አባላት እና ዕዳ ጠያቂዎች በመዋሃዱ ወይም በመከፋፈሉ የተስማሙበት መሆኑ፤ ወይም



ለ) ያልተስማሙ አባላትና ዕዳ ጠያቂዎች የተከፈላቸው መሆኑ ወይም የክፍያ ዋስትና የተሰጣቸው መሆኑ ተረጋግጦ ልዩ ውሣኔው አግባብ ባለው ባለሥልጣን የተመዘገበ መሆኑ፤

ሐ) የቀድሞው የኅብረት ሥራ ማህበራት ወይም ኅብረት ሥራ ማህበር ምዝገባ ከመዝገብ ማሰረዙ እና በውህደት ወይም በመከፈሉ የተፈጠረ የኅብረት ሥራ ማህበራት ወይም የኅብረት ሥራ ማኅበር

10/ Whereas the cooperative society suspended pursuant to sub-article (9) of this Article fails to apply within 30 consecutive days to lift up the suspension, the appropriate authority may take legal liquidation measure.

11/ Where the General Assembly of a cooperative society suspended pursuant to sub-articles (9) of this Article submits its request to lift up the suspension and where the appropriate authority found the request appropriate, it may lift up the suspension. If the appropriate authority doesn't lift up the suspension, it shall give a written explanation. Any party dissatisfied by the decision rendered at the federal level may lodge petition to The Federal High Court or if the decision is rendered at regional level may lodge petition to the appropriate court which has jurisdiction.

## 11. Juridical Personality and Responsibility

1/ Any cooperative society registered in pursuance of Article 10 of this Proclamation shall have juridical personality from the date of its registration.

2/ Any cooperative society shall not be liable beyond its total asset; and it has limited liability.

## 12. By-laws of a Cooperative Society

1/ Any cooperative society shall have its own by-laws; and the contents of the by-laws shall include the following particulars:

a) name and address of the cooperative society;
b) objectives and activities of the cooperative society;
c) working place and area of the cooperative society;
d) requirements necessary for membership of the cooperative society;
e) the rights and duties of members of the cooperative society;

መመዝገቡ፤

ሲረጋገጥ ይሆናል፡፡

፫/ በወህደቱ ህልወናቸውን ያጡ የኅብረት ሥራ ማህበራት መብት እና ግዴታዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት በተመዘገበው የኅብረት ሥራ ማህበር ልዩ ወሳኔ ላይ በተመለከተው ዝርዝር መሠረት አዲስ ወደ ተቋቋመው የኅብረት ሥራ ማህበር ይተላለፋሉ፡፡

፬/ በመከፋፈሉ ሕልወናውን ያጣው የኅብረት ሥራ ማህበር መብት እና ግዴታዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት በተመዘገበው የኅብረት ሥራ ማኅበሩ ልዩ ውሣኔ ላይ በተመለከተው ዝርዝር መሠረት አዲስ ወደ ተቋቋመት የኅብረት ሥራ ማኀበራት ይተላለፋሉ፡፡

## ፲፬. ስለ ኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን አደረጃጀት

፩/ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን ተመሳሳይ ዓላማ ባላቸው ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት ይደራጃሉ፡፡

፪/ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬንን በፌደራል ወይም በክልል ደረጃ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አዋጭነቱ እየታየ ማደራጀት የሚቻል ይሆናል፡፡

፫/ በፌደራል ደረጃ የሚደራጁ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን አባላት ቢያንስ ከሁለት ክልሎች የተውጣጡ መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት መሆን አለባቸው፡፡

## ፲፭. ስለ ኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን አደረጃጀት

፩/ ተመሳሳይ ዓላማ ባላቸው ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን ይደራጃል፡፡



፪/ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አዋጭነቱ ታይቶ የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽንን በፌደራል ወይም በክልል ደረጃ ማደራጀት ይቻላል፡፡

፫/ በፌደራል ደረጃ የሚደራጅ የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን አባላት ቢያንስ ከሁለት ክልሎች የተውጣጡ ሁለት እና ከዚያ በላይ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች መሆን አለባቸው፡፡

## ፲፮. በሙያ የሚደራጅ የኅብረት ሥራ ማህበር ማሟላት ያለበት ማስፈርቶች

፩/ ማንኛውም መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበር የአባላትን ሙያ መሠረት አድርጎ የሚደራጅ ከሆነ እያንዳንዱ አባል ከሚመለከተው አካል የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ማሰረት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የሚቀርብባቸው በህግ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ እንዲያወጡ በሚያስገድዱ የስራ ማስኮች ብቻ

f) the powers, responsibilities and duties of management bodies;

g) conditions for withdrawal and dismissal from membership;

h) conditions for election, appointment, term of office and suspension or dismissal of the members of the management committee or other management bodies;

i) conditions for calling of meeting and voting procedures of the cooperative society;

j) allocation and distribution of profit;

k) auditing;

l) employment of workers;

m) other particulars not contrary to this proclamation, and regulation and directive for the implementation of this proclamation.

2/ By-laws of a cooperative society may be amended by the special resolution of the general assembly; provided, however, that the amendment of the by-laws of the society shall be effective on the date of its submission to and registration by the appropriate authority.

3/ Where the cooperative society decides on the amendment of its by-laws three copies of the amendment and the special resolution of the cooperative society general assembly made in accordance with this Proclamation shall be submitted to appropriate authority within 15 consecutive working days from the date of the decision. If the by-law amended is not submitted to appropriate authority within the specified period it shall not be accepted.

4/ The appropriate authority shall register the amendment to the cooperative society where it is satisfied that the amendment of the by-laws specified in sub-article (3) of this Ariticle was made in accordance with this Proclamation and regulation and directive

ላይ ይሆናል፡፡

፫/ የሚያ የኅብረት ሥራ ማህበራት እሴት ጨምረው ለሚያመርቱት ምርት ወይም ለሚሰጡት አገልግሎት የጥራት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማቅረብ አለባቸው፡፡

## ፲፯. ስለ የኅብረት ሥራ ማህበራት ሊግ አደረጃጀት

፩/ የዚህ አዋጅ እና የሌሎች ሕጎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራትን፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖችን እና ፌዴሬሽኖችን በኢትዮጵያ ወስጥ የሚወክል ሊግ በአገር አቀፍ ደረጃ ሊመሠርቱ ይችላሉ፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚመሰረት ሊግ ቁጥር ከአንድ ሊበልጥ አይችልም፡፡

፫/ የሊግ አደረጃጀት፣ ተግባራትን እና የፋይናንስ ምንጭ በተመለከተ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይሰወናል፡፡

፱ሺ፬፻ ፶፫

## ፲፰. የኅብረት ሥራ ማህበራት ግዴታ

የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖራቸዋል፦

፩/ የኅብረት ሥራ ማህበራት አባሎቻቸው የሚፈልጉትን አገልግሎት በተያዘው ዕቅድ መሠረት የማቅረብ፤

፪/ በአገሪቱ የአሠሪና ሠራተኛ ሕግ መሠረት ለቀጠሯቸው ሠራተኞች መብታቸውን የማጠበቅ፤

፫/ የኅብረት ስራ ማህበራት ከሚያገኙት ገቢ ላይ ከገቢ ግብር በስተቀር ሌሎች ለመንግስት መክፈል የሚገባቸውን ክፍያ በሕጉ መሠረት ወቅቱን ጠብቀው ገቢ የማድረግ፤

፬/ የመተዳደሪያ ደንቡን አክብሮ የማስራት፤

፭/ ለሚመለከተው አካል አስፈላጊውን መረጃ በተጠየቀ ጊዜ የማስጠት፤

፮/ የተቋቋሙበትን መርህ እና ዓላማ አክብረው የማስራት፡፡

## ፲፱. ሥራ ስለመጀመር

፩/ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወር ውስጥ በዕቅዱ መሠረት ሥራ ካልጀመረ በተጨማሪ በሦስት ወር ወስጥ እንዲጀምር ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፡፡

፪/ የኅብረት ሥራ ማህበሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በተሰጠው የማስጠንቀቂያ ጊዜ ወስጥ ሥራ ካልጀመረ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ሂሣብ ከተጣራ

issued for the implementation of this Proclamation, and give evidence of its registration within five consecutive working days.

5/ If the appropriate authority fails to register the amendment or fails to notify the cooperative society the reasons for not registering within five consecutive working days, the amended by-laws shall be considered as registered and put to practice.

6/ Any cooperative society shall include principles and values of the cooperative society in its by-laws.

7/ Any cooperative society shall include requirements necessary to encourage participation of female members in the management committee of the society.

8/ any cooperative society shall include activities to increase the active participation of women, youth and the disabled in their strategic and annual plans.

## 13. Amalgamation and Division of Cooperative Societies

1/ The general assembly of a cooperative society through a special resolution may;

a) divide itself into two or more cooperative societies, or

b) amalgamate with one or more cooperative societies and form a new cooperative society.

2/ The special resolution on the amalgamation or division of a cooperative society shall be effective upon verifying that:

a) the members and creditors of the cooperative society are agreed on the amalgamation or division;

እና መፍረሱ ከተወሰነ በኋላ ምዝገባው ተሰርዞ ሕጋዊ ሰውነቱን እንዲያጣ ይደረጋል፡፡

**፲፫. <u>የምዝገባ ምስክር ወረቀትን ስለማሳደስ</u>**

፩/ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በዚህ አዋጅ መሠረት ተቋቁሞ ከተመዘገበበት እና ሕጋዊ ሰውነት ካገኘበት ቀን ጀምሮ አግባብ ያለው ባለሥልጣን ባወጣው መመሪያ መሠረት በየሦስት ዓመቱ የምዝገባ ምስክር ወረቀቱን ማሳደስ አለበት፡፡



፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የምዝገባ ምስክር ወረቀት ያላሳደሰ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር አግባብ ባለው ባለሥልጣን በሚያወጣው መመሪያ መሠረት እርምጃ ይወሰድበታል፡፡

**፲፬. <u>የኅብረት ሥራ ማነበራት ተግባራትና ኃላፊነቶች፤</u>**

፩/ የኅብረት ሥራ ማነበራት በየደረጃቸው በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (፪) እስከ (፱) የተመለከቱት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖራቸዋል፡፡

፪/ መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማነበራት በዋናነት ግለሰብ አባላት በተናጠል መወጣት የማይችሉትንና ከአቅማቸዉ በላይ የሆነን የጋራ ኢኮኖሚያዊና ማነበራዊ ችግር መፍታት የሚችሉ ተግባራት ላይ የሚያከ ናውኑ ሆኖ በተለይ የሚከተሉትን ያካትታል፡-

ሀ) ለአካባቢው ህብረተሰብ ስለኅብረት ሥራ ማነበር ፅንሰ ሃሳብ ግንዛቤ ማስጨበጥ እና ቅስቀሳ የማድረግ፤

ለ) በአካባቢ ልማት እና ጥበቃ ሥራ ላይ የመሳተፍ፤

ሐ) ለአባላት በቅድመ ምርት እና በድህረ ምርት ላይ ስለምርት ጥራት ሥልጠና የማስጠት፤

መ) ለአባላት የመጋዘን አገልግሎት የማስጠት፤

ሠ) የአባላትን ችግር የሚፈቱ ፕሮጀክቶችን የመንደፍ፤

ረ) የአባላትን ምርት በመረከብ ዕሴት በመጨመር አባል ለሆኑባቸው ዩኒዬን ወይም ፌዴሬሽን የማስረከብ ወይም የተሻለ የገበያ መዳረሻ በማፈላለግ የመሸጥ፤

ሰ) ሌሎች በመተዳደሪያ ደንባቸው ላይ የተዘ ረዘሩትን ተግባራት የማከናወን።

፫/ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒየኖች በዋናነት አባል መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማነበራት በተናጠል መወጣት

b) the members and creditors that did not agree have been paid off or the payment guarantee determined in the special resolution is registered by appropriate authority;

c) the registration of the former cooperative societies or cooperative society has been canceled from the register and the newly amalgamated or divided cooperative societies are registered.

3/ The rights and duties of cooperative societies which have lost their identities by amalgamation shall be transferred to the newly formed cooperative society as specified in the special resolution passed pursuant to sub-article (2) of this Article.

4/ The rights and duties of a cooperative society which has lost its identity by division shall be transferred to the newly formed cooperative societies as specified in the special resolution passed pursuant to sub-article (2) of this Article.

**14. <u>Establishment of Cooperative Societies Union</u>**

1/ A cooperative societies union shall be establish by two or more primary cooperative societies having similar objectives.

2/ Cooperative societies union may be established at the federal or regional levels based on their social and economic feasibility.

3/ The members of a cooperative societies union established at federal level shall be drawn at lest from two regional primary cooperative societies.

**15. <u>Establishment of Cooperative Societies Federation</u>**

